የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፸፫
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፬ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 73
ADDIS ABABA 1st June 2011

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፪፻፵፮/፪ሺ፫
የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያዎች ተመኖች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ………………………………ገፅ ፭ሺ፱፻፳፩

**CONTENTS**

**Regulation No. 246/2011**
Commercial Registration and Business Licensing and Related Services Fees Tariffs Council of Ministers Regulation …. ………………………………………… Page 5921

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፮/፪ሺ፫**

**የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያዎችን ተመኖችን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፮/፪ሺ፪ አንቀጽ ፷፪ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያዎች ተመኖች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፮/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ:-

፩/ "አዋጅ" ማለት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፮/፪ሺ፪ ነዉ፤

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተመለከቱት ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No.246/2011**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO DETERMINE FEE TARIFFS FOR COMMERCIAL REGISTRATION AND BUSINESS LICENSING AND RELATED SERVICES**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 62 of the Commercial Registration and Business Licensing Proclamation No. 686/2010.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as "Commercial Registration and Business Licensing and Related Services Fees Tariffs Council of Ministers Regulation No.246/2011".

**2. Definitions**

In this Regulation:

1/ "Proclamation" means Commercial Registration and Business Licensing Proclamation No. 686/2010;

2/ the definitions provided for under Article 2 of the Proclamation shall apply to this Regulation.

ያንዱ ዋጋ
Unit price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,001

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

በዚህ ደንብ የተመለከቱት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያዎች ተመኖች ተፈፃሚ የሚሆኑት በንግድ ሚኒስቴር እና ሚኒስቴሩን በመወከል በክልል ቢሮዎች ወይም በሌሎች የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሚሰጡ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እና ተያያዥ አገልግሎቶች ነው፡፡

## ፬. የአከፋፈል ሁኔታ

፩/ በዚህ ደንብ የተመለከቱት የአገልግሎት ክፍያዎች በተናጠል እና አገልግሎቶቹ በተጠየቁ ጊዜ መከፈል አለባቸው፡፡

፪/ ለንግድ ፈቃድ ማውጣት ወይም እድሳት የሚፈፀሙ ክፍያዎች ለእያንዳንዱ የንግድ ፈቃድ አይነት ለየብቻ መከፈል አለባቸው፡፡

## ፭. የክፍያ መጠን

በዚህ ደንብ መሠረት የሚፈፀሙ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እና ተያያዥ አገልግሎቶች ክፍያዎች ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ በተቀመጡ ተመኖች መሠረት ይከፈላሉ:-

**የንግድ ምዝገባና ፈቃድ እና ተያያዥ አገልግሎቶች የክፍያ ተመኖች**

| ተ.ቁ. | የአገልግሎቱ አይነት | የክፍያ መጠን /በብር/ |
|---|---|---|
| 1 | የአገልግሎት መጠየቂያ የማመልከቻ ቅጽ | 2 |
| 2 | የንግድ ምዝገባ | 100 |
| 3 | የንግድ ምዝገባ ዕድሣት | 100 |
| 4 | የንግድ ምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ | 80 |
| 5 | ምትክ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት | 50 |
| 6 | የንግድ ምዝገባ ስረዛ የምስክር ወረቀት | 50 |
| 7 | የንግድ ምዝገባ በመዝገብ የሰፈረው ዝርዝር ቅጂ ወይም የተውጣጣ መረጃ ቅጂ ወይም በንግድ መዝገብ ያልተመዘገበ ለመሆኑ ወይም የንግድ ምዝገባው የተሰረዘ ለመሆኑ ማረጋገጫ | 100 |
| 8 | የንግድ መደብር ቅርንጫፍ አድራሻን ለመዝጋቢው መሥሪያ ቤት ለማሳወቅ | 50 |
| 9 | የንግድ ስም ምዝገባ ማጣሪያ | 25 |
| 10 | የንግድ ስም ምዝገባ | 100 |
| 11 | የንግድ ስም ምዝገባ ለውጥ ወይም | 80 |
| 12 | ምትክ የንግድ ስም ምዝገባ የምስክር ወረቀት | 50 |
| 13 | የንግድ ስም ምዝገባ ስረዛ የምስክር ወረቀት | 50 |

## 3. Scope of Application

Commercial registration and business licensing and related services fees tariffs prescribed in this Regulation shall be applicable for commercial registration and business licensing and related services to be delivered by the Ministry of Trade and regional bureaus or other federal government offices on behalf of the Ministry.

## 4. Mode of Payment

1/ The services fees provided in this Regulation shall be paid separately and whenever the services are demanded.

2/ Payments to be made for the issuance or renewal of business licenses shall be paid separately for each type of business license.

## 5. Rates

Payments to be made pursuant to these regulations for commercial registration and business licensing and related services shall be paid in accordance with rates prescribed in the following schedule:

**Commercial Registration and Business Licensing and Related Services Fees Tariffs**

| No. | Types of Services | Amount (in Birr) |
|---|---|---|
| 1 | Service request application form | 2 |
| 2 | Commercial registration | 100 |
| 3 | Renewal of commercial registration | 100 |
| 4 | Alteration or amendment of commercial registration | 80 |
| 5 | Substitute commercial registration certificate | 50 |
| 6 | Commercial registration cancellation certificate | 50 |
| 7 | Copy of entry of registration or extract from or no entry in the commercial register certificate or certificate of cancellation of the commercial registration | 100 |
| 8 | Informing the registering office the address of the branch of a business | 50 |
| 9 | Verification of the registration of a trade name | 25 |
| 10 | Registration of trade name | 100 |
| 11 | Alteration or amendment of a trade name | 80 |
| 12 | Substitute of a trade name registration certificate | 50 |
| 13 | Certificate of cancellation of a trade name registration | 50 |

| | | |
|---|---|---|
| 14 | የንግድ ፈቃድ ለማውጣት | 100 |
| 15 | የንግድ ፈቃድ ዕድሣት | 100 |
| 16 | በንግድ ፈቃድ ላይ ለሚደረግ ለውጥ ወይም ማሻሻያ | 80 |
| 17 | ምትክ የንግድ ፈቃድ | 50 |
| 18 | የንግድ ፈቃድ ስረዛ የምስክር ወረቀት | 50 |
| 19 | የማስፋፊያና የማሻሻያ ፈቃድ | 100 |
| 20 | የንግድ እንደራሴ የምስክር ወረቀት | 250 |
| 21 | የንግድ እንደራሴ የምስክር ወረቀት ዕድሣት | 250 |
| 22 | የንግድ እንደራሴ የምስክር ወረቀት ለውጥ ወይም ማሻሻያ | 100 |
| 23 | ምትክ የንግድ እንደራሴ የምስክር ወረቀት | 100 |
| 24 | የንግድ እንደራሴ የምስክር ወረቀት ስረዛ ማረጋገጫ | 100 |
| 25 | ህዝቡ አክስዮን ለመግዛት በመፈረም ለሚቋቋም የአክሲዮን ማኅበር መስራቾች ለሚሰጥ ፈቃድ | 100 |
| 26 | በውጭ ሀገር የኢትዮጵያን የንግድ ትርኢት ለማዘጋጀት ለሚሰጥ ፈቃድ ወይም የውጭ ሀገር መንግሥት ወይም ድርጅት በሚያደርገው የውጭ ሀገር የንግድ ትርኢት ኢትዮጵያ ተካፋይ እንድትሆን ተሣታፊ ዎችን ለማስተባበር ለሚሰጥ ፈቃድ | 300 |
| 27 | በውጭ ሀገር በሚዘጋጅ የንግድ ትርኢት የግል ተሳትፎ ለማድረግ ለሚሰጥ ፈቃድ | 100 |
| 28 | በውጭ ሀገር መንግሥት ወይም ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚዘጋጅ የውጭ ሀገር ምርት የንግድ ትርኢት ፈቃድ | 300 |
| 29 | በሀገር ውስጥ በሚዘጋጅ የንግድ ትርዒት ውስጥ በውጭ ሀገር መንግሥት ወይም በውጭ ሀገር ነጋዴ የግል ተሳትፎ ለማድረግ ለሚሰጥ ፈቃድ | 100 |

፮. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፳፬ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

| | | |
|---|---|---|
| 14 | Issuance of a business license | 100 |
| 15 | Renewal of a business license | 100 |
| 16 | Alteration or amendments made to a business license | 80 |
| 17 | A substitute business license | 50 |
| 18 | Certificate of cancellation of a business license | 50 |
| 19 | Expansion and upgrading permit | 100 |
| 20 | Certificate of commercial representative | 250 |
| 21 | Renewal of certificate of commercial representative | 250 |
| 22 | Alteration or amendments made to certificate of commercial representative | 100 |
| 23 | Substitute of a certificate of commercial representative | 100 |
| 24 | Certificate of cancellation of certificate of commercial representative | 100 |
| 25 | Permit to founders of a share company to be established by a public subscription | 100 |
| 26 | Permit given to organize Ethiopian trade exhibition in a foreign country or permit to coordinate participants to facilitate Ethiopia's participation in a foreign trade exhibition organized by a foreign state or organization | 300 |
| 27 | Permit to privately participate in a foreign trade exhibition to be held abroad | 100 |
| 28 | Permit for trade exhibition to be organized in Ethiopia by a foreign state or organization to display foreign products | 300 |
| 29 | Permit to privately participate in a locally organized trade exhibition by a foreign state or by a foreign business person | 100 |

6. **Effective Date**

This Regulation shall come in to force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta

Done at Addis Ababa this 1st day of June, 2011.

**MELES ZENAWI**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**